NOV 12 /2002

# ለምን ይበደራሉ?? ለምን ያበድራሉ

(የቢቢሲ ራድዮ ጋዜጠኛ ህዳር ሶስት ቀን 1995 አ.ም. ካቀረበው ትችት የተተረጎመ)

ኢትዮጵያ በውጭ ርዳታ የመተማመን የረጅም ጊዜ ታሪክ ያላት አገር ነች። ይህም ሆኖ ለረጅም ጊዜ በእዳና በድህነት ደረጃ አሉታዊ የሆነ ግንኙነት ሲንጸባረቅ ቆይቱዋል። ከውጭ የሚመጣ እዳ እየጨመረ በሄደ ቁጥር የህዝቡ የነፍስ ወከፍ ገቢ እዛው ባለበት ሲረግጥ ታይቱዋል። ድህነት ተስፋፍቱዋል። ድህነት ከፍቱዋል። በአፍሪካ ደረጃ እንኩዋን ሃገሪቱ ወደሁዋላ በመቅረቱዋ ኢትዮጵያ በዚች ባልታደለች አህጉር ላሉት ችግሮች ሁሉ እንደምሳሌነት መጠቀስ የምትችል አገር ለመሆን በቅታለች።

ታዲያ አሁንስ ለምን ትበደራለች? አለም አቀፋዊ የፋይናንስ ተቋዋሞችስ በፊት የተሰጠው ብድር ምንም ፋይዳ እንዳላመጣ እያዩ በየጊዜው ተጨማሪ ብድር ለመስጠት የሚገፋፋቸው ነገር ምንድን ነው?

የኢትዮጵያ መንግስት ደግሞ ደጋግሞ የሚያቀርበው ምክንያት ድህነትን ለመዋጋት ብድር ያስፈልገኛል የሚል ምክንያት ነው። ለዚህም ሃገር ስላላበሰ ድህነት፤ ስለርሃብ፤ ስለ በሽታ፤ ስለ ሁዋላ ቀር የእርሻ ዘዴ፤ ስለ ኤይድስ፤ ስለመጠነ ሰፊ ስራ አጥነት የታወቁና ጸሃይ የሞቃቸው አሃዞችን በየጊዜው ይደረድርና እነዚህን ሁሉ ለመዋጋት ብድርና እርዳታ ያስፈልገኛል ይላል። ነገር ግን ያለፉት ብድሮች ካስወጡት ወጭ አንጻር ምን ጥቅም አስገኝተዋል የሚለውን ጥያቄ ምንጊዜም አይመልስም።

በዚህ ላይ ደግሞ እንደኢትዮጵያ ባሉ አገሮች መንግስታት የሚጠናወታቸው የበታችነት ስሜት አለ። በራሳቸው የማይተማመኑ መንግስታት ከውጭ አበዳሪ ተቋዋማት ጋር ሲዳሩ መታየታቸው በህዝቦቻቸው ፊት ተቀባይነት የሚጨምርላቸው ይመስላቸዋል። ይህ ደግሞ የስልጣን ዘመናችንን ለማራዘም ይጠቅመናል ብለው ያምናሉ። እነዚህ ተቋዋማት በሚያዘጋጁዋቸው አለም አቀፍ ስብሰባዎች ላይ ከሌሎች እኩል መታየታቸው የአለም አቀፉ ህብረተሰብ ሌጂቲሜት አባላት እንዲመስሉ ይረዳቸዋል። እንደዚህ አይነቶቹን መድረኮች በሃገራቸው ውስጥ ተቃዋሚዎች ላይ የአፈና ዘመቻ ለመክፈት ይጠቀሙባቸዋል።

ከዚህ አልፈውም ይሄዳሉ። የነዚህ አለም አቀፍ ተቋዋማት ባልደረቦች መንግስታቱ በሃገራቸው በመከተል ላይ ስላሉት ፖሊሲ አወንታዊ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ይጠቀሙባቸዋል። እነዚህንም ሪፖርቶች ለሚከተሉት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ትክክለኛነት ማረጋገጫ አድርገው ያቀርቡዋቸዋል። ይህንን በተደጋጋሚ አንብበናል። ሰምተናል። የኢትዮጵያ መንግስት በመሬትም ሆነ በጎሳ ፌዴሬሽን ጉዳይ የሚከተለውን ፖሊሲ እንዴት አለም ባንክና የአለም የገንዘብ ድርጅት (አይኤምኤፍ) እንዳደነቁለት በኩራት ሲገልጽ አይተነዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የአለም አቀፍ ተቋዋማት አላማ አለ። እነዚህ ተቋዋማት ከነዚህ መንግስታት ጋር ሲደራደሩ ሙሉ በሙሉ የበላይነት እንዳላቸው ያውቃሉ። እነዚህ መንግስታት ያለባቸውን ያለመረጋጋትና በቁዋፍ የመኖር ስሜት የራሳቸውን አጀንዳ ለማራመድ ይጠቀሙበታል። አንድ መንግስት ይበልጥ ያልተረጋጋና ይበልጥ በቁዋፍ ያለ ሲሆን ለአበዳሪዎቹም የዚያኑ ያህል የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጥራል። እነዚህ ተቋዋማት ዞሮ ዞሮ ዋና ጥቅማቸው ከዛሬ ነገ ይበልጥ ማበደር ነው። ጥቅማቸው በድሆች አገሮች የኢኮኖሚ ልማት እንዲመጣ መስራት ሳይሆን ከበለጸጉት አገሮች በኤክስፖርት ስም በድሆች አገሮች ሸቀጥ ማራገፍ ነው።

ይህንን አላማ ለማራመድና ሁልጊዜ ይበልጥ የማበደር ሽሽግና እውነተኛ አጀንዳቸውን ለማድበስበስ  በምሁራን፤ በባለሙያ ፈሊጥ የተሸፋፈነ ዲስኩራቸውንና ሪፖርቶቻቸውን ይደረድራሉ። የቆዩ ፕሮግራሞችን አንዴ መዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም፣ አንዴ ፖሊሲ ማስተካከያ፤ አንዴ ዘርፍ ማስተካከያ፤ አንዴ ዘርፋዊ መልሶ ማቋዋቋዋሚያ፤ አንዴ አስቸኩዋይ መልሶ ማቋዋቋዋም የሚል ስም እየሰጡ መልሰው መልሰው ያንኑ ፕሮግራም ለማቅረብ ይሞክራሉ።

በኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ በተከታታይ መንግስታት ስር ሲካሄድ የቆየው የመበደር ታሪክ እስካሁን ድረስ ልማትን በማምጣትም ሆነ ድህነትን በመቀነስ መስክ ያመጣው ነገር የለም።እንዲያውም ይበልጥ መበደር ሃገሪቱን ወደ ይበልጥ ድህነት እንድትዘፍቅ አርጉዋታል ማለት ይቻላል። እንደቡና አይነቶቹን የውጭ ንግድ ሸቀጦች በመሸጥ የሚገኘው ገቢ እየቀነሰ ሲሄድ ከዚህ እየቀነሰ ከሚሄድ የውጭ ምንዛሪ ሃገሪቱ ይበልጥ እየጨመረ የሚሄድ ክፍል ለብድር መክፈያ ታወጣለች። በዚያው ልክ ደግሞ ለሃገር ልማትና ድህነትን ለመቀነስ አስፈላጊ የሆነውን የውጭ ምንዛሪ እዳ ለመክፈል ትጠቀምበታለች።

የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ እንደሚባለው አበዳሪዎቹ በዚህ ሁሉ ላይ ብድርን እንደውጭ ፖለቲካ ማራመጃ መሳሪያ አድርገው ይጠቀሙበታል። ይህ ደግሞ በኢትዮ/ኤርትራ ጦርነት ጊዜ አበዳሪዎችና ርዳታ ለጋሾች ኢትዮጵያ ብድርም እርዳታም ከማግኘቱዋ በፊት ፖለቲካ አቁዋሙዋን እንድታለሰልስ ጫና ለማድረግ ሲሞክሩ በግልጽ የታየ ነበር። ጥገኝነቱ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ለባእዳን ጫናና እጅ ጥምዘዛ መመቻቸት የግድ ነውና።